**የአስተዳደር ወሰንና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ስለመሆኑና ስለሚያስከትላቸው ጦሶች!**

**መግቢያ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በተደጋጋሚ የሚታዩ የማንነትና የወሰን ጉዳዮችን ሃገራዊ በሆነ፣ በማያዳግም ሁኔታ እና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መፍትሔ በማፈላለግ ለመፍታት በሚል ምክንያት **ጊዜያዊ ኮሚሽን ለማዋቀር የሚያስችል አዋጅ** በማርቀቅ ይፀድቅለት ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም በቀረበው ረቂቅ አዋጁ ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ ለዝርዝር ዕይታ ለውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች እና በተባባሪነት ለሕግ፣ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሰጠው ውሳኔ የሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ህልውናና በዚህ አገር እጣ ፈንታ ላይ ወሳኝ ድርሻ ያለው ነው።

ረቂቁ አዋጁ እንደሚያስገነዝበው የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዋናነት ጎልተው የወጡና በጠቅላይ ሚኒስቴሩ፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በፌደሬሽን ምክር ቤት የሚመሩለትን የማንነት፣ ወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳቦች ለፌደሬሽን ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ የሚያቀርብ ጊዜያዊ ኮሚሽን ስለሚመሰረትበት ሁኔታ በረቂቅ ሕጉ ላይ ደንግጓል፡፡

በረቂቁ አዋጁ ስር **ለኮሚሽኑ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር በሕገ-መንግስቱ መሰረት ለክልል ምክር ቤትና ለፌደሬሽን ምክር ቤት የተሰጠ ስልጣንና ተግባር ነው**፡፡ በረቂቁ አዋጅ መሰረት **ኮሚሽኑ የማንነትንና የወሰን ጉዳዮችን በተመለከተ ወሳኝ ሚና አለው**፡፡ በሕገ-መንግስቱ መሰረት የማንነት ጥያቄ የራስን እድል በራስ የመወሰንና የማስተዳደር መብት አካል ሆኖ አተገባበሩ በዋነኛነት የክልሎች ስልጣን ነው፡፡ ክልሎች አጥጋቢ መፍትሔ ያልሰጡበት እንደሆነ በይግባኝ የፌደሬሽን ምክር ቤት እንደሚወስነው በግልፅ ተቀምጧል፡፡ የሕገ-መንግሰቱ አንቀፅ 39፣ 52(2) (ሀ) እና 62 (3) ላይ ተመልክቷል፡፡ የክልሎች የወሰን ጉዳይን በተመለከተ ጥያቄ በተነሳ ጊዜ በቅድሚያ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክልሎች ተነጋግረው በመስማማት የሚፈቱት ሲሆን የሚመለከታቸው

ክልሎቹ መስማማት ካልቻሉ ግን የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንደሚሰጥበት የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 48 እና 62(6) ያስገነዝባል፡፡

በመሆኑም ይህ ረቂቅ አዋጅ በዚህና ከዚህ በታች በዝርዝር በተመለከቱት ሌሎች ብዙ ሁኔታዎች (ምክንያቶች) **የሃገሪቱ የበላይ ሕግ የሆነውን ሕገ-መንግስት ይጥሳል፡፡** የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 9(2) እንደሚያስገነዝበው ደግሞ ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖች ሕገ-መንግሰቱን የማስከበርና ለሕገ-መንግሰቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ እንዲሁም የሕገ-መንግሰቱ አንቀፅ 13(1) እንደደነገገው በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች በሕገ-መንግሰቱ ምዕራፍ ሶስት ስር የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ማንኛውም ዜጋ፣ በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌደራል መንግስትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖች ሕገ-መንግሰቱን የማክበር ብቻ ሳይሆን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡

ስለሆነም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በብዙ ሁኔታዎች ሕገ-መንግስቱን ባለማክበር (በመጣስ) የአስተዳደር ወሰንና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ያዘጋጀ በመሆኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **ረቂቅ አዋጁን ባለማጽደቅ ሕገ-መንግስቱን የማክበር ብቻ ሳይሆን የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታውን ሊወጣ ይገባል፡፡** እኛም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሕገ-መንግስቱን እንዲያከብር የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለብን፡፡ ይህንንም ግዴታችን መወጣት ከሚያስችሉን መንገዶች አንዱና ዋነኛው ረቂቅ አዋጁ ኢ ሕገ-መንግስታዊ ነው የሚያሰኙትን ዝርዝር ምክንያቶችን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጹሁፍም ሆነ በማናቸውም ሌላ አመቺ መንገድ በማሳወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ኃላፊነታችን ለመወጣት ያስችለን ዘንድ በዚህ ጹሁፍ አማካኝነት ረቂቅ አዋጁ **ሕገ-መንግስቱን የጣሰ ነው የምንልባቸውን ዝርዝር ነጥቦችን እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡**

1. ***<u>የረቂቅ ህጉ ዓላማ ሕገ መንግስቱን የሚፃረር ስለመሆኑ</u>***

*የረቂቅ ዓዋጁ መሰረታዊ ዓላማ በረቂቁ አንቀፅ* 4 *ሰፍሯል። ከዚህ በተጨማሪ ለህጉ መነሻ የሆኑ ሌሎች ሀሳቦችም በረቂቅ አዋጁ መግቢያ ላይ ይገኛሉ። የረቂቅ አዋጁ የመጨረሻ ግብ እነዚህን ጉድዮች አጣምሮ በማየት መገንዘብ ይቻላል። ያስቀመጠው አጠቃላይ አቅጣጫ ሕገ-መንግስቱን የተከተለ አይደለም። ይሉቁንም የሕገ-መንግስቱን መሰረታዊ መንፈስ የሳተ፣ የብሄር ብሄረሰቦችን መብት መና የሚያስቀር፣ የክልሎችና የፌደሬሽን ምክር ቤት ስልጣን የሚጥስና* ***የፌደራል አስፈፃሚው አካል በህዝቦች መብት ላይ የወሳኝነት ሚና እንዲኖረውና አድራጊ ፈጣሪ እንዲሆን የሚያደርግ ነው።*** *ይህን ለማሳየት በረቂቁ መግቢያ በሚገኙ አንዳንድ ክፍሎችና ዓላማው ላይ ያሉ ችግሮች ለአብነት እንደሚከተለው ቀርበዋል።*

1.1 *የረቂቅ ዓዋጁ መግቢያ ሁለተኛው አንቀፅ* ***"በክልሎች የአስተዳደር ወሰን፣ ራስን በራስ ማስተዳደርና በማንነት ጥያቄዎች ዙርያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮችን <u>አገራዊ</u> በሆነና <u>በማያዳግም</u> መንገድ መፍታት በማስፈለጉ፣"*** (ስርዝ የተጨመረ) *የሚል ክፍል አለው። ይህ የረቂቁ ክፍል የሕገ-መንግስቱን መንፈስና ግልፅ ሀሳቦች ባለማወቅ ወይም ሆን ብሎ የዘነጋ ነው። የማንነት ጉዳይ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ* 39 *መሰረት መሰረታዊ ከሚባሉት መብቶች አንዱ ነው። ይህ መብት ደግሞ የተሰጠው ለብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ብቻ ነው። በየትኛውም የሰለጠነ የፍትህ ስርዓት የመብት ጉዳይ መብቱ አለኝ በሚል ወገን ጥያቄው ሲነሳ የሚስተናገድ ነው። የማንነት መብትም በተመሳሳይ በሚመለከተው ባለመብት ሲቀርብ ስልጣን ባለው አካል የሚታይ እንጂ በአስተዳደራዊ ሂደት "የማያዳግም" መፍትሄ የሚሰጠው አይደለም። ኮሚሽኑ እንደታሰበው ስራውን ቢያከናውን እንኳን ከዛ በኋላ ጥያቄ አለኝ የሚል ብሄር ቢኖር ጉዳዩ ከአሁን ቀደም ብሎ የማያዳግም ውሳኔ ስለተሰጠው ጥያቄ ማንሳት አትችልም ሊባል አይችልም። ከዛም ባሻገር የማንነትና የወሰን ጉዳዮች ተጨባጭ ሁኔታ ግምት ውስጥ እየገባ በሚመለከታቸው ክልሎች ውሳኔ የሚሰጥባቸው ናቸው። ይህም ማለት የግጭት አፈታት ስርዓቱ በራሱ ብዝሀነትን የሚያንፀባርቅ በመሆኑ (አንቀፅ* 48 *ይመለከተዋል) ረቂቁ እንደሚመኘው የማንነትና የወሰን ጉዳዮች "አገራዊ" "መፍትሄ" የሚሰጣቸው አይደሉም። ለጉዳዮቹ የሚያስፈልገው አገራዊና የማያዳግም*

መፍትሄ በሕገ-መንግስቱ የሰፈረው ስርዓት ነው። ስርዓቱ ተግባራዊ የሚሆነው ደግሞ ሕገ-መንግስቱ ስልጣን በሰጣቸው አካላት ብቻ ነው። ስለዚህ ረቂቅ አዋጁ የማንነትና የወሰን ጥያቄዎች መሰረታዊ ባህርይ ስላልተገነዘበ ወይም ሆን ብሎ ስለተወ ከተሳሳተ መነሻ የሚጀምር ነው። በዚህም ምክንያት ሊያሳካ የፈለገው ጉዳይ ሕገ-መንግስቱ ካስቀመጠው ስርዓት እጅጉን የራቀ ነው።

1.2 በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 48 መሰረት የፌደሬሽን ምክር ቤት ወሰንን በማስመልከት ስልጣን የሚኖረው በክልሎች መካከል የወሰን ግጭት ካለና ክልሎቹ ጉዳዩን በስምምነት መፍታት ካልቻሉ ብቻ ነው። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ሕገ-መንግስቱ ሁሉንም የወሰን አለመግባባቶች በሚመለከት ስልጣን ለፌደሬሽን ምክር ቤት አለመስጠቱን ነው። እንደሚታወቀው የአስተዳደር ወሰን አለመግባባት በክልሎች ደረጃ ብቻ ሳይሆን በዞን ደረጃ በሚገኙ ብሄረሰቦች መካከልም ሊከሰት ይችላል። ሆኖም ሕገ-መንግስቱ የወሰን ጉዳይ ወደ ፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲመራ የሚፈቅደው በክልሎች መካከል ያለ የወሰን አለመግባባት ከሆነ ነው። ከዚህ ውጭ የሚከሰቱ የወሰን ጥያቄዎች በፌደሬሽን ምክር ቤት ስልጣን ውስጥ የሚካተቱ አይደሉም። ስለሆነም በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 52(1) መሰረት በአንድ ክልል ውስጥ የሚነሱ የወሰን ጉዳዮች የክልል ስልጣን ናቸው ማለት ነው። ረቂቅ አዋጁ ግን ይህን ልዩነት ከቁብ ሳይቆጥር ሁሉንም የወሰን ጉዳዮች የፌደራል መንግስት ስልጣን እንደሆነ ታሳቢ አድርጎ ተነስቷል። ይህ አቀራረብ በሕገ-መንግስቱ የሰፈረውን ግልፅ የስልጣን ክፍፍል ቀመር የሚጥስ ስለሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

1.3 ከዚህም ሌላ ረቂቅ አዋጁ መግቢያው ላይ ***"ከአስተዳደር ወሰን ጋር ተያይዞ የሚነሱ ውዝግቦች በተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መሃል የቅራኔ ምንጭ መሆናቸውን በመገንዘብ፣"*** የሚል ክፍል ይዟል። ይህም አባባል ቢሆን ሕገ-መንግስቱ ታሳቢ ካደረጋቸው እሴቶች እጅጉን የራቀ ነው። ሕገ-መንግስቱ በተለያዩ ብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መካከል ቅራኔ የሚፈጠረው ማንነታቸው ህጋዊ እውቅና ሲነፈግ፣ ራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸው የተሸራረፈ እነደሆነ፣ ስልጣን የህዝብ መሆኑ ሲዘነጋ በዚህም ምክንያት መልካም አስተዳደር ሲጠፋ፣ የግለስብ መብቶች ሲጣሱ፣ የህግ የበላይነት ሲናድ፣ የልማት ራዕይ ሲጨናገፍ ነው። ሕገ-መንግስቱ የወሰን ጥያቄ

ሲነሳ ምላሽ የሚያገኝበትን ስርዓት ከመዘርጋቱም በላይ የወሰን ጉዳይ ከማንነት ጋር እንዲያያዝ ያደረገ በመሆኑ በህዝቦች መካከል የዘላቂ ቅራኔ ምክንያት ሊሆን ይችላል የሚል መነሻ የለውም። ስለዚህ በረቂቁ የቀረበው ምናባዊ መነሻ ውጤቱን የሚተነብይ ከመሆኑም ባሻገር (ቅራኔ የበዛው በወሰን ችግር ምክንያት ነው? የሚለው ጥያቄ ገና የኮሚሽኑን "ሳይንሳዊ" ጥናት የሚሻ በመሆኑ) ሕገ-መንግስቱ ምላሽ የሰጠውን ጉዳይ እንደ አዲስ ለመፈተሽ የሚዳዳው ነው።

1.4 ረቂቅ አዋጁ አሉ ያላቸውን ቅራኔዎች *"ገለልተኛ በሆነ፣ ከፍተኛ ሞያዊ ብቃት ባለውና ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ ማፈላለግ አስፈላጊ ሆኖ"* መገኘቱን መግቢያው ላይ ይገልፃል። ይህም መነሻ የሕገ-መንግስቱን መርህ በግልፅ የሚጥስ ነው። ሕገ-መንግስቱ የማንነትና የወሰን ጉዳዮች ገለልተኛ ናቸው ተብለው በአስፈፃሚው በሚሾሙ ሙያተኞች ሳይሆን የጉዳዩ ባለቤቶች አባል በሆኑባቸው ፌደሬሽን ምክር ቤትና በክልል ምክር ቤቶች እንደሚታይና እንደሚወሰን ግልፅ አቋሙን በተለያዩ አንቀፆች አስቀምጧል። የማንነት ጉዳይ ልዩ ትኩረት የተሰጠውና የሕገ መንግስቱ መለያ ባህርይ በመሆኑ ጉዳዩ ከሞያተኞች ይልቅ በፖለቲካ ሂደት፣ ከአስፈፃሚው ይልቅ የህዝቦች ውክልና በሚታይባቸው ተቋማት እልባት እንዲያገኝ በሕገ-መንግስቱ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ጉዳይ ነው። ለማስታወስ ያህል ሕገ-መንግስቱ በሚረቅበት እና በሚፀድቅበት ጊዜ የማንነትን ጥያቄ ጨምሮ የሕገ-መንግስት ትርጉም ጉዳዮች በሞያተኞች እንዲታዩ ሀሳብ ቀርቦ የነበረ ቢሆንም ሀሳቡ ለአገራችን ሰላምና ዘላቂ እድገት አይበጅም ተብሎ ስለታመነበት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። ስለዚህ ረቂቁ በግልፅ ውድቅ የተደረገን ሃሳብ እንደ አዲስ በማቅረብ በሞተ ነገር ላይ ህይወት ለመዝራት የሚጥር ነው። የሚገርመው ነገር ሕገ-መንግስቱን በጣሰ መንገድ የማንነትና የወሰን ጉዳዮችን ለማስተናገድ የተዘጋጀ ረቂቅ መሰረታዊ ቅራኔዎች *"ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍትሄ"* ያገኛሉ የሚል ግምት መያዙ ነው። ዘላቂ ሰላም ማረጋገጥ የሚቻለው ሕገ-መንግስቱን በመከተል እንጂ ሕገ-መንግስቱን የሚጥስ ቀመር ተግባራዊ በማድረግ አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

1.5 የረቂቁ አንቀፅ 4 የህጉ ዓላማ *"ኮሚሽኑ አሳታፊ፣ ግልጽ፣ አካታችና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከአስተዳደር ወሰኖች፣ ራስን በራስ ማስተዳደር እና ከማንነት ጋር የተያያዙ*

*ግጭቶችንና መንስኤያቸውን በመተንተን የመፍትሄ ሃሳቦችን ለህዝብ፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና ለአስፈጻሚው አካል ማቅረብ ነው።"* በማለት ይደነግጋል። በረቂቁ ላይ የሰፈረው ይህ ዓላማ ቢያንስ በሶስት ምክንያቶች ሕገ-መንግስቱን የሚጥስ ነው። አንደኛው ለሌሎች አካላት የተሰጠን ስልጣን ለኮሚሽኑ የሚሰጥ መሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ግጭቶችን ለመፍታት የሚጠቀምባቸው መስፈርቶች ከሕገ-መንግስቱ እውቅና ውጭ መሆናቸው ነው። ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ ሕገ-መንግስቱ የማያውቀውን አዲስ የአለመግባባት መፍቻ ስነስርዓት የሚያበጅ መሆኑ ነው። ቀጥሎ ሶስቱንም አንድ በአንድ እንመልከት።

1.6 ከላይ እንደተገለፀው የማንነትና የወሰን ጥያቄዎችን በሚመለከት ሕገ መንግስቱ ግልፅ የስልጣን ክፍፍል ቀመር ዘርግቷል። በዚህ መሰረትም የማንነትና የወሰን ጉዳዮች በቅደም ተከተል በክልሎችና በፌዴሬሽን ምክር ቤት እንዲወሰን ደንግጓል። (የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 39፣ 46፣ 47፣ 48፣ 62 ይመለከተዋል) ከአሁን ቀደም የተነሱ የማንነትም ይሁን የወሰን ጉዳዮች በዚሁ ስርዓት እልባት እንዲያገኙ በማድረግ አለመግባባቶች የሚፈቱበት ትክክለኛ ስርዓት እንደሆነ ተረጋግጧል። በዚህ ሂደት ስርዓቱ እርግጥም የሰላም ዋስትና መሆኑ ተረጋግጧል። ወደፊት የሚነሱ የማነንትም ይሁን የወሰን ጥያቄዎች ካሉ የተሻለው አማራጭ ውጤታማነቱ በተረጋገጠው ስርዓት መሰረት ማስተናገድ እንጂ አዲስ ኢ ሕገ-መንግስታዊ መላምት ይዞ መቅረብ አይደለም። የቀረበው ረቂቅ በህዝብ የፀደቀን የስልጣን ክፍፍል ወደ ጎን በመተው የማንነት ጥያቄዎች የሕገ-መንግስት ስልጣን የሌላቸው የአስፈፃሚው አካላት እንዲሳተፉበት የሚፈቅድ ነው። የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 48 ***"የክልሎችን ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች ስምምነት ይፈፀማል። የሚመለከታቸው ክልሎች መስማማት ካልቻሉ የፌደሬሽን ምክር ቤት የህዝብን አሰፋፈርና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ይወስናል"*** ይላል። የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 62 በሌላ በኩል ከአንቀፅ 39 እና በክልሎች መካከል ያለን አለመግባባት የመፍታት ስልጣን የፌደሬሽን ምክር ቤት እንደሆነ ይደነግጋል። ረቂቅ ህጉ ይህን በመተላለፍ የአስፈፃሚው አካል በዚህ ሂደት እንዲሳተፍ ስልጣን የሚሰጠው ረቂቅ አቅርቧል። የህግ ልዕልና ሁሉም የመንግስት አካላት በተሰጣቸው ስልጣን ክልል

ውስጥ ብቻ ሆነው መስራትን የሚጠይቅ ነው። በመሆኑም ረቂቅ አዋጁ የህግ ልዕልናን መሰረተ ሀሳብና የሕገ-መንግስቱን ግልፅ ድንጋጌ የሚጥስ ዓላማ ያነገበ በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

1.7 ሕገ-መንግስቱ የማንነትም ይሁን የወሰን ጥያቄዎች የሚስተናገዱበትን ስርዓት አስፍሯል። ይህ የሆነው የማንነት ጥያቄዎች የሚስተናገዱበት ስርዓት የውጤቱን ያህል ጠቀሜታ ስላላቸው ነው። ሕገ-መንግስቱ የማንነት ጥያቄ ሲቀርብ ጥያቄው የሚስተናገድበት ቀመር አስቀምጧል። በሕገ-መንግቱ መሰረት የማንነት ጥያቄ ለብሄር ብሄረሰብና ህዝብ ከተሰጠው መብት የተያያዘ ነው። የማንነት ውሳኔ የአንድን ብሄረሰብ ማንነት የሚወስን ነው ማለት ነው። አንቀፅ 39 ላይ እንደሰፈረው ማንነት የሚገለፀውም ሆነ የሚረጋገጠው የጋራ ጠባይ በሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምድ፣ በጋራ መግባቢያ ቋንቋ፣ የጋራ ህልውና አለን በሚል እምነት፣ በስነ ልቦና አንድነትና በተሳሰረ መልክአምድር በመኖር ነው። ይህ መመንዘር የማይፈልግና የማይተካ የማንነት የህግ መስፈርት ነው። ስለዚህ የማንነት ጥያቄ የሚመለሰው በዋናነት በዚህ የህግ መስፈርት መሰረት ብቻ ነው። ረቂቅ አዋጁ ግን ይህን ሕገ-መንግስታዊ አቋም በመጣስ የማንነት ጥያቄዎች በህግ ሳይሆን ***"ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ"*** መፍትሄ ማፈላለግን እንደ ዓላማ ይዟል። ረቂቅ አዋጁ ይህን **ያህል ግልፅ በሆነ መንገድ የሕገ-መንግስት ጥሰት ለማወጅ የደፈረበት ምክንያት መገመት የሚቻል ነው፡፡** ይህ አካሄድ አደገኛና የሕገ-መንግስቱን መሰረታዊ መነሻ የሚጥስ በመሆኑ በምንም መለኪያ ቢሆን ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም።

1.8 መሰረታዊ መብት የሆነው ማንነት ተራ አስተዳደራዊ ጉዳይ እንደሆነ ተቆጥሮ በረቂቅ ህጉ ለአስፈፃሚው አካል ተጠሪ በሆነ ኮሚሽን የመፍትሄ ሀሳብ እንዲቀርብበት ተፈልጓል። ይህ ሂደት የማንነት ጥያቄ በሚመለከተው ህዝብ ሳይሆን በሌላ ማንኛውም አካል እንዲቀርብ በመፍቀድ የሕገ-መንግስቱን መሰረታዊ ስሌት መና የሚያስቀር ነው። በህዝብ ተቀባይነት ካገኘው ስርዓት የተለየ ስርዓት መቅረፅ ለምን አስፈለገ የሚል ጥያቄ እንዲነሳ ያደርጋል። ለማንኛውም የረቂቅ አዋጁ ዓላማ በግልፅ ሕገ-መንግስቱን የሚያሽመደምድ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም። ህጉ ቢፀድቅም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም።

## 2. ኮሚሽን ስለማቋቋም (አንቀጽ 3)

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 3(1) እንደደነገገው የአስተዳደር ወሰንና የማንነት ጉዳዮች ኮሚሽን በዚህ አዋጅ ተቋቋሟል፡፡ የዚህ ኮሚሽን ስልጣንና ተግባር በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 5 እና 6 ስር የተደነገገ ሲሆን በዚህም መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት የማንነትና ወሰን ጉዳዮች ኮሚሽን እንዲቋቋም ሕግ የማርቀቅ ስልጣን የለውም፡፡ የፌደሬሽን ምክር ቤት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 62 የተሰጡትን ስልጣንና ተግባሮች በመወጣት ረገድ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ነው ብሎ ካመነ ሕገ-መንግስቱን ባከበረ መልኩ ሕግ አርቅቆ ይጸድቅለት ዘንድ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ ስልጣን አለው፡፡ በመሆኑም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከአስፈጻሚነት የስልጣን ማዕቀፉ ውጭ በሆነ ጉዳይ ላይ (ማለትም በሕገ-መንግስት አንቀጽ 62 መሰረት ለፌደሬሽን ምክር ቤት በተሰጡ ስልጣንና ተግባሮች ላይ) ሕግ የማርቀቅ ስልጣን የለውም፡፡ ይህ ሆኖ እያለ ማርቀቁ የሚያሳየው የሚኒስትሮች ምክር ቤት አንቀጽ 77(11)ን መጣሱን ነው፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም የማንነትና የወሰን ጉዳዮች ኮሚሽን የማቋቋሚያ አዋጅ የማውጣት የሕገ-መንግስት ስልጣን የለውም፡፡ አገሪቱ በምትከተለው የፌደራላዊ ስርአት አወቃቀር መሰረት ሕገ-መንግስቱ የፌደራልና የክልል መንግስታትን የስልጣን ክፍፍል በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት የፌደራል መንግስት ማንነትና የወሰን ጉዳዮች በሚመለከት በሕግ ለመወሰን የሚያስችል አንዳችም ስልጣን የለውም (ሕገ-መንግስቱ ዓንቀፅ 51 እና 55 ላይ ተመልክቷል)፡፡ ምክንያቱም አንደኛ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 82 እና 84 መሰረት በሕገ- መንግስታዊ ጉዳዮች ላይ የፌደሬሽን ምክር ቤትን የሚያማክር ተቋም ማለትም የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ተመስርቷልና ነው፡፡ በመሆኑም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አዋጅ በማወጅ ለሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የተሰጠን ስልጣን ለሌላ አካል መስጠት አይችልም፡፡

ሁለተኛ የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 62(2) እንደሚያስገነዝበው የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤን አደረጃጀት የመወሰን ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በዚህም አግባብ ስራውን ለመወጣት የሚያስችለው አደረጃጀት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ እንዲኖረው በማድረግ ስራውን መወጣት ይችላል፡፡ አደረጃጀቱንም በራሱ እንዲወስን ስልጣን የተሰጠው ያለማንም ጣልቃ ገብነት በሕገ- መንግስቱ መሰረት እንዲወጣ ለማስቻል ነው፡፡

ሶስተኛ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 62(10) መሰረት የፌደሬሽን ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ያለ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሁንታ ቋሚም ሆነ ጊዚያዊ ኮሚቴዎች የማቋቋም ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ነው፡፡ በዚህም መሰረት የፌደሬሽን ምክር ቤት በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 62 የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለመወጣት ይረዳው ዘንድ ቋሚም ሆነ ጊዚያዊ ኮሚቴ (ዎች) የማቋቋም ሙሉ ስልጣን አለው፡፡

በተለይም በሕገ-መንግሰቱ የፌደሬሽን ምክር ቤትን የሚያማክር ተቋም ተቋቁሞ እያለ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህ ስልጣን ለሌላ አካል እንዲሰጥለት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን የጠየቀበት ምክንያት እጅግ አደገኛ እንድምታ አለው፡፡

በመሆኑም የአዋጁ አንቀጽ 3 የሕገ-መንግስቱን አንቀጽ 82፣ 84፣ 62(10) እና 77(11)ን የጣሰ ነው፡፡ ስለሆነም አዋጁ ቢታወጅ እንኳን በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 9(1) መሰረት በተግባር ተፈጻሚነት የለውም፡፡

## 3. <u>የአዋጁ ዝርዝር ድንጋጌዎች እንደምታ</u>

ከላይ እንደተገለፀው የአዋጁ ዓላማና ሌሎች መነሻዎች የሕገ-መንግስቱን ግልፅ ድንጋጌዎች የሚጥሱ ናቸው። ከተሳሳተ ዓላማ የሚመነጩ ድንጋጌዎች ከዚህ የተለየ ገፅታ ይኖራቸዋል ተብሎ አይገመትም። ሆኖም ከግምት በላይ በእርግጥም ረቂቅ ዓዋጁ ኢ. ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች የያዘ መሆኑን ለማሳየት ያህል የረቂቅ አዋጁ አንዳንድ ክፍሎች እንደሚከተለው ተዳሰዋል።

### 3.1 የኮሚሽኑ ስልጣንና ተግባር (አንቀጽ 5)

ረቂቅ አዋጁ ለኮሚሽኑ የሰጠው ስልጣን በሕገ-መንግስቱ ለሌሎች አካላት የተሰጠ በመሆኑ ረቂቁ በሕገ-መንግስት የሰፈረውን የስልጣን ክፍፍል የሚያፈርስ ነው። ለአብነት ያህል የኮሚሽኑን ስልጣን የሚመለከቱ አንዳንድ ድንጋጌዎች መመልከት ይበቃል።

(1) *“ ከአስተዳደራዊ ወሰኖች አከላለል፣ ራስን በራስ ማስተዳደር እንዲሁም ከማንነት ጥያቄ ጋር የተገናኙ ማናቸውንም ችግሮችንና ግጭቶችን በጥናት ለይቶ አማራጭ*

*የመፍትሄ ሃሳቦችን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል”*

**አስተያየት (የንዑስ አንቀጽ 1)**

በዚህ ድንጋጌ ስር ኮሚሽኑ ማናቸውንም አይነት ችግሮችና ግጭቶችን (ከማንነት፣ ወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ችግሮችንና ግጭቶችን ጨምሮ) በጥናት በመለየት በሕገ-መንግስቱ ውስጥ ከተቀመጡት መፍትሄዎች ወይም እስካሁን ከተሰጡት መፍትሄዎች አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለጠቅላይ ሚኒስተሩና ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት የማድረግ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይህም ማለት፡-

አንደኛ ኮሚሽኑ ማናቸውንም ችግሮችና ግጭቶችን በራሱ ተነሳሽነት የማንሳትና የማጥናት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ኮሚሽኑ ከማንነት፣ ወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ችግሮችንና ግጭቶችን በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት አጥንቶ አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችን ነድፎ ለጠቅላይ ሚኒስተሩና ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት የማድረግ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም **ባለመብቱ ሳይጠይቅ ኮሚሽኑ በራሱ ጊዜ ማየት ይችላል፡፡**

ይሁንና በሕገ-መንግስቱ መሰረት ከባለመብቱ ውጭ ሌላ ሰው ወይም አካል ባለመብቱን ተክቶ የማንነት ጥያቄ ሆነ ሌላ ጥያቄ የመጠየቅና ፍትህ የማግኘት መብት የለውም፡፡ ለምሳሌ ያህል፣ የማንነት ጥያቄን በተመለከተ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 39/5/ እና በአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀፅ 19/1/ ላይ እንደተመለከተው ለጥያቄው መነሻ በሆነው ነገር ወይም ጥያቄው በተመሰረተበት ጉዳይ ላይ መሰረታዊ መብት ያለው የማንነት ማህበረሰብ ካልሆነ በስተቀር የማንነት ጥያቄ የመጠየቅም ሆነ ፍርድ የማግኘት መብት የለውም፡፡ በመሆኑም ከሚመለከተው የማንነት ማህበረሰብ ውጭ የሆነ አካል የማንነት ጥያቄ እንዲጠይቅ አይፈቀድለትም፣ ሊፈቀድለትም አይገባም፡፡

ይህም ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የማንነት ጥያቄ የመጠየቅ መብት የሌለው ወገን (ሰው) (ማህበረሰብ) የማንነት ጥያቄ ከመነሻው እንዳያቀርብ ማድረጉ ቢያንስ ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ የዚህ መርህ አንደኛው ጠቀሜታ አንድ መሰረታዊ መብት ከተጎናፀፈው ማህበረሰብ ወይም አካል በቀር ሌላ ሰው/ሰዎች ጥያቄ እንዳያቀርቡ ለማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም በመብቱ የመጠቀም ወይም ያለመጠቀም ጉዳይ የባለመብቱ ብቻ በመሆኑ ነው፡፡ የማንነት ጥያቄ የመብት

ማስከበር (ማንነት የማስከበር) ጉዳይ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የሕግ መብት ከመነሻው ከሌለው መብት ማስከበር ብሎ ነገር የለም፡፡ መብት የሌለው ሰው/ማህበረሰብ መብቴ ይከበርልኝ ብሎ ቢጠይቅ የጊዜና የሃብት ብክነትን ከማስከተሉ በቀር በሂደቱ በስተመጨረሻ የሚጠይቀውን ዳኝነት በሕገ-መንግስቱ በተቀመጠው መልክ ቅርፅ አግባብ ሊያገኘው አይችልም፡፡ በአጠቃላይ የመብት ጥያቄ የሚያቀርበው ደግሞ ባለመብቱ እንጂ ሌላ ሰው ሊሆን አለመቻሉ የህግ መሰረታዊ መርህ ነው። የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 39 ይህን ጉዳይ በግልፅ ይዟል። ረቂቅ ዓዋጁ ይህን መርህና የሕገ-መንግስት ድንጋጌ በመጣስ የማንነት ጉዳይ በጥናት የሚወሰን አካዳሚክ ጉዳይ እንዲሆን የሚያደርግ ነው። የማንነትን ጥያቄ የሚነሳው በሚመለከተው ህዝብ ሳይሆን በኮሚሽኑ አጥኚዎች እንዲሆን የሚያደርግም ነው። በመሆኑም ይህ ሁኔታ ደግሞ የሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 39/5/ን፣ 39(3)ን ፣48ን እና ሌሎችንም ድንጋጌዎች ይጥሳል፡፡

ሁለተኛ ኮሚሽኑ አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለጠቅላይ ሚኒስተሩና ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት የማድረግ ግዴታ ተጥሎበታል፡፡ እዚህ ላይ መታየት ያለበት ነጥብ አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦች ምን ማለት ነው የሚለውን ነው፡፡ አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦች የሚለው አነጋገር በሕገ-መንግስቱ ውስጥ ከተቀመጡት የመፍትሄ ሃሳቦች ወይም በሕገ-መንግስቱ መሰረት እስካሁን ከተሰጡት መፍትሄዎች አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦች ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ረቂቅ አዋጁ ሕገ-መንግስታዊ መፍትሄዎችን አይቀበልም፡፡ ይህም ማለት ኮሚሽኑ ከዚህ ቀደም እልባት ያገኙ የማንነት፣ ወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮችን በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት አጥንቶ ከዚህ ቀደም ከተሰጡት መፍትሄዎች የተለዩ የመፍትሄ ሃሳቦችን ነድፎ ለጠቅላይ ሚኒስተሩና ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሪፖርት የማድረግ ስልጣን ተሰጥቶታል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ረቂቅ አዋጅ የሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 9(1)፣ አንቀፅ 39/5/ን፣ 39(3)ን፣ 48ን እና ሌሎችንም የሕገ-መንግስቱን ድንጋጌዎችን ይጥሳል፡፡

> ***(2) "በህዝቦች እኩልነትና ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ስር እንዲሰድና እንዲዳብር ለማድረግ "ሊወሰዱ ስለሚገባቸው እርምጃዎች ማሻሻያ" ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት "ምክረ ሃሳቦችን" ያቀርባል ይላል"፡፡***

**አስተያየት (የንዑስ አንቀጽ 2)**

በመሰረቱ ይህ ስልጣን በሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 62(4) መሰረት ለፌደሬሽን ምክር ቤት የተሰጠ ስልጣን ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ድንጋጌ ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ነው፡፡ ከዚህም በላይ፣ ይህ ድንጋጌ ኮሚሽኑ አንድነት ስር እንዲሰድ ሊወሰዱ የሚገባቸውን የማሻሻያ እርምጃዎችን በተመለከተ ምክረ ሃሳቦችን ለጠቅላይ ሚኒስተሩና ለፌደሬሽን ምክር ቤት እንዲያቀርብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ ይህም የሚያሳየው ከዚህ ቀደም የተወሰዱ እርምጃዎችን የማሻሻል ፍላጎት መኖሩን ነው፡፡

*(3) "አስተዳደራዊ ወሰኖች" በቀጣይነት የሚወሰኑበትንና የሚለወጡበትን መንገድ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን ሕገ-መንግስታዊ "መርህዎች" ያገናዘበ፣ "ግልፅና ቀልጣፋ ስርዓት" ወይም "የህግ ማሻሻያ" እንዲዘረጋ ጥናት በማድረግ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት "ምክረ ሃሳብ" ያቀርባል ይላል፡፡*

**አስተያየት(የንዑስ አንቀጽ 3)**

በዚህ ድንጋጌ መሰረት አስተዳደራዊ ወሰኖች ወደፊት በተከታታይ እንደ አዲስ ስለሚወሰኑበትና ስለሚለወጡበት መንገዶች ኮሚሽኑ በማጥናት ምክረ ሃሳቡን ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲያቀርብ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ በመሆኑም ይህ ድንጋጌ የረቂቅ አዋጁ መግቢያ ላይ የወሰን ጉዳዮችን በማያዳግም መልኩ መፍታት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ አዋጅ ሊረቀቅ ችሏል በማለት ከገለፀው ጋር ፍፁም ተቃራኒ ነው፡፡

*(4) "ጎልተው የወጡና በፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በፌዴራል መንግስት የሚመሩለትን የአስተዳደራዊ ወሰን ውዝግቦችን መርምሮ የውሳኔ ሃሳብ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እና ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል"፣*

**አስተያየት(የንዑስ አንቀጽ 4)**

ይህ ድንጋጌ የአስተዳደር ወሰን ውዝግቦችን የሚሉ ቃላት የተጠቀመ ቢሆንም እነዚህ ቃላት ከአዋጁ አንቀጽ 2(1) አኳያ ስንመለከተው የማንነት፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶችን ይይዛሉ፡፡ በመሆኑም ኮሚሽኑ ጎልተው የወጡ የማንነት፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶች በፌደራሉ መንግስት፣ በፌደሬሽን ምክር ቤት ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲመራለት ተቀብሎ

በመመርመር የውሳኔ ሃሳቡን ለጠቅላይ ሚኒስተሩና ለፌደሬሽን ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡

በዚህም መሰረት በዚህ ድንጋጌ ስር የሚሸፈኑት ጎልተው የወጡ የማንነት፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶች ብቻ ናቸው፡፡ እንዲሁም በአዋጁ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው አዋጁን ለማውጣት ያስፈለገበት ዋና ምክንያት በክልሎች የአስተዳደር ወሰን፣ ራስን በራስ የማስተዳደርና በማንነት ጥያቄዎች ዙርያ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮችን መፍታት በማስፈለጉ ነው፡፡ በተጨማሪም የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15 የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን በመሰረቱ እስከ 3 ዓመት ድረስ ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩት ኮሚሽኑ የተወሰኑ የተለዩ የማንነት፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶች ብቻ በፌደራሉ መንግስት፣ በፌደሬሽን ምክር ቤት ወይም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመርተውለት በመመርመር የውሳኔ ሃሳቡን ለጠቅላይ ሚኒስተሩና ለፌደሬሽን ምክር ቤት የማቅረብ ጊዚያዊ ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም ነው፡፡ ይህም ማለት የተወሰኑ የማንነት፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶች በተለየ ሁኔታ እንዲስተናገዱ የሚደራጅ ተቋም ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 39፣ 62(4)፣ 88(1)፣ 88(2) እና ሌሎቹም ድንጋጌዎች ስር ስለብሄሮች እኩልነት የተደነገገውን ሕገ-መንግስታዊ መርሆ ይንዳል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ድንጋጌ ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ነው፡፡

እንዲሁም በዚህ ድንጋጌ ስር የፌደራሉ መንግስት፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት ወይም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት **በራሳቸው ፍቃድ ጎልተው የወጡ የማንነት**፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር ጉዳዮች እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ክስተቶችን ኮሚሽኑ እንዲያያቸው የማቅረብ ስልጣን በተናጠል ተሰጥቷቸዋል፡፡ በመሆኑም ባለመብቱ ሳይጠይቅ የፌደራሉ መንግስት፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት ወይም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በራሳቸው ፍቃድ ጎልተው የወጡ የማንነት፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ስለሆነም ይህ ረቂቅ አዋጅ የሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 9(1)፣ አንቀፅ 39/5/ን፣ 39(3)ን ፣48ን እና ሌሎችንም የሕገ-መንግስቱን ድንጋጌዎችን ይጥሳል፡፡

(5) ***"ከአስተዳደራዊ ወሰኖች ጋር በተያያዘ የተነሱ ግጭቶች ተፈተው፣ በአጎራባች ክልሎች መሃከል ያለው መልካም ግንኙነት የሚታደስበትና የሚጠናከርበትን መንገድ ያመቻቻል"፣***

**አስተያየት የንዑስ አንቀፅ 5**

ከላይ እንደተገለፀው ኮሚሽኑ ሕገ-መንግስቱን የጣሰ አሰራር እንዲከተል ተፈልጓል። በዚህ መንገድ የክልሎችን መልካም ግንኙነት ማደስና ማጠናከር ይቻላል (ለዛውም ሶስት ዓመት ብቻ በሚቆይ ኮሚሽን) ብሎ ማሰብ የለየለት የዋህነት ነው።

**(6) *"በቀጣይነት" አስተዳደራዊ ወሰኖች "የግጭት መንስዔ" እንዳይሆኑ ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች አስመልክቶ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምክረ ሃሳብ ያቀርባል"፡፡***

**አስተያየት (የንኡስ አንቀጽ 6)**

የዚህ ድንጋጌ መነሻ በአጠቃላይ በአገሪቱ ላይ እየታዩ ያሉት ግጭቶችና ችግሮች ዋነኛ ምንጭ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 46(2)፣ 39(5) እና 48 የተመለከቱት የማንነትና ወሰን ጉዳዮች አፈታት ስርዓቶች እንደሆኑ አድርጎ የመውሰድ አዝማሚያ እጅግ የተዛባ እና አደገኛ የሆነ አረዳድና ድምዳሜ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

**(7) *"አስተዳደራዊ ወሰኖችና አካባቢያቸው አስተማማኝ ሰላም የሰፈነባቸው የልማትና የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድባቸው እንዲሆኑ አስተዳደራዊ ወሰኖችን የተመለከተ "የፖሊሲ ማእቀፍ" ያመነጫል"***

**አስተያየት (የንዑስ አንቀጽ 7)**

በዚህ ድንጋጌ ስር ኮሚሽኑ ሕገ-መንግስታዊ የፖሊሲ ማዕቀፍ (constitutional policy frame work) እንዲያመነጭ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡ አዋጁ በዋነኛነት የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን ለመተግበር እንዲመች ተደርጎ የተበጀ የክልሎች ወሰን አከላለል መስፈርትን እንደ ስጋትና የግጭቶች መንስኤ አደርጎ የሚገነዘብ መሆኑ የተሳሳተ አረዳድ ነው፡፡ የኮሚሽኑ መመስረት የሕገ-መንግስቱ አንኳር የሆኑትን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች መብቶችን እና

ጠንካራ ክልሎች የያዘ የፌደራል ስርአት የማነፅ ጅምር ተሰፋን የመናድ እድሉ ከፍ ያለ ነው፡፡ አሁን ያለው አካሄድ የክልሎችን ስልጣንና ህልውና ወደ ጎን የተወና ብሔሮች እና ብሔረሰቦች የተጎናፀፉትን እውቅናና የስልጣን ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት በቅጡ ያልተገነዘበ እንደሆነ የሚያሳዩ ብዙ መገለጫዎች አሉት፡፡ ፌደራላዊ ስርአቱ እንዲመሰረት ብዙ ውይይቶች እንደተደረገና ከዛም በኋላ የብዙ ፖሊቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ስነ-ልቦናዊ ስራዎች መነሻ እንደነበር እንገነዘባለን፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ አሁን ያለው የክልሎች አወቃቀር እንደ አዲስ እንዲታይ የሚያስችል ስርዐት/ፖሊሲ ማበጀት ማለት ማለቂያ የሌላቸው ግጭቶችን ማስከተሉና ብሎም የፌደሬሽኑን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ሌላ የባሰ ቀውስ ይጋብዛል፡፡ በተጨማሪም ያሉትን ተቋማት ለማጎልበትና ለማሻሻል ሊደረግ የሚገባውን እድል ያጠባል፡፡ ይህ ሁኔታና ሂደት መቋጫ ወደ ሌላው ግጭት ሊከተን ይችላል፡፡

(8) ***"የአስተዳደር ወሰን ጉዳዮችን በተመለከት የህዝብ አስተያየት ይሰበስባል"፣***

***(9) "ጉዳዮ ከሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል የስራ ኃላፊዎች፣ የፖለቲካ ቡድኖች፣ እንዲሁም ሌሎች ባላድርሻ አካላት አሰተያየትና ለጥናቱ የሚሆን ግብአት ይሰበስባል"፣***

***(10) "ከህዝብ ግብዓትና አስተያየት የሚሰበሰብበትን አካሄድ የሚያሳይ፣ ሂደቱ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል ያካተተ መሆኑ የሚያረጋግጥ ስትራተጂና ዝርዝር እቅድ ያዘጋጃል"፡፡***

**አስተያየት (የንዑስ ዓንቀፅ 8፣ 9 እና 10)**

በንኡስ አንቀፅ 8 እና 9 የተገለፁት ጉዳዮች ረቂቁ የሕገ-መንግስቱን ጤነኛ አካሄድ ወደጎን በመተው የወሰን ጉዳዮች ላይ ድራማ ለመስራት ዝግጅት መጀመሩን የሚያረጋግጡ ናቸው። እንደሚታወቀው "ህዝብ" የሚለው ቃል በሕገ-መንግስቱ የራሱ የሆነ ትርጉም የያዘ ነው። የማንነትና የወሰን ጥያቄ ሲነሳ የህዝብ ድምፅ እንዴት እንደሚስተናገድም ግልፅ ስነ-ስርዓት ተቀምጧል። ረቂቅ አዋጁ "ህዝብ" የሚለውን ቃል ትርጉም ያልሰጠው በመሆኑ ውዝግቡ የማይመለከታቸው ሰዎች በህዝብ አስተያየት ስም ተሳትፈው ውጤቱን ፌደራል አስፈፃሚው አካል ወደሚፈልገው አቅጣጫ እንዲያመዝን ለማድረግ የታሰበ ነው። **የድፍረቱ ድፍረት ሕገ-መንግስቱ** ውስጥ ምንም ድርሻ የሌላቸውን ***"ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል የስራ ኃላፊዎች፣***

*የፖለቲካ ቡድኖች፣ እንዲሁም ሌሎች ባላድርሻ አካላት”* አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ የወሰን ክርክር በሁለት አካላት መካከል የሚፈጠር ውዝግብ ነው። መፈታት የሚችለውም ሁለቱም አካላት በሚያቀርቡት ክርክርና ማስረጃ ብቻ ነው ረቂቅ አዋጁ ግን በአሳታፊነት ስም የማይመለከታቸው አካላት በማያገባቸው ጉዳይ ገብተው ነገሩን ይበልጥ እንዲወሣበራ ይፈቅዳል። ከዚህም ሌላ ሕገ-መንግስቱ ወሰን በአሰፋፈርና በህዝብ ፍላጎት ብቻ ይወሰናል የሚለውን ግልፅ ድንጋጌ (አንቀፅ 48) በመተው በማይመለከታቸው ሰዎች **አስተያየት ለውሳኔው መነሻ እንዲሆን በር ይከፍታል**። ይህ ሂደት የህዝብን የስልጣን ባለቤትነት የሚንድ አደገኛ አካሄድ ነው። ከተለመደው የውዝግብ አፈታት ስርዓት ያፈነገጠም ነው።

**3.2 የአስተዳደር ወሰንናየማንነት ጥያቄዎች (አንቀጽ 6)**

***“ማንኛውም የአስተዳደር ወሰን ውሳኔ፣ ራስን በራስ ማስተዳደርና የማንነት ጥያቄ በኮሚሽኑ ተጠንቶ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ እልባት ያገኛል”፡፡***

**<u>አስተያየት</u>**

**<u>የማንነት ጉዳዮች በተመለከተ</u>፡-** በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጎልቶ ያልወጡ የማንነት ጥያቄዎችም ጭምር በኮሚሽኑ ተጠንተው (በራሱ ተነሳሽነት ጭምር) በቀጥታ ለፌደሬሽን ምክርቤት ቀርበው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡ ይሁንና በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 52(2)(ሀ) ስር ክልሎች የማንነት ጉዳዮች በመጀመርያ ደረጃ የመወሰን ስልጣን አላቸው፡፡ ይህም ስለመሆኑ የፌደሬሽን ምክር ቤት በስልጤ ጉዳይ ላይ አስገዳጅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በመሆኑም ክልሎች በክልላቸው ውስጥ በሚነሱ የማንነት ጥያቄዎች ላይ ያላቸውን የመጀመሪያ የመወሰን ስልጣን ተቀምቷል፡፡

እንዲሁም ባለመብቱ መብቱ እንዲከበርለት ጥያቄ ባላቀረበበት ሁኔታ ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት የማንነት ጥያቄዎችን በማንሳት መርምሮ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣን አለው፡፡ በተጨማሪም ድንጋጌው ኮሚሽኑ የማንነት ጥያቄ የማቅረብ መብት ጨርሶ የሌለው አካልን ጥቆማ/ጥያቄን መነሻ ያደረገ ምርመራ እንዲያደርግ የሚያደርግ አካሄድ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ድንጋጌ በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 37 እና አንቀፅ 39/5/ ስር ስለፍትህ የመጠየቅና የማግኘት መብት የተደነገጉት ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን ይጥሳል፡፡

በተጨማሪም እልባት ያገኙ የማንነት ጥያቄዎችን እንደገና ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት አጥንቶ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣን

አለው፡፡ ይህም <u>ማናቸውም የአስተዳደር ወሰን ውሳኔ</u> በማለት አመላክቷል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ስር ማናቸውም የአስተዳደር ወሰን ውሳኔ የሚሉት ቃላት ከአዋጁ አንቀጽ 2(1) አኳያ ስንመለከተው የማንነት፣ የወሰንና ራስን በራስ የማስተዳደር እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ጉዳዮች ውሳኔዎችን ያካትታል፡፡ በመሆኑም የማንነት ጉዳዮች ውሳኔዎችም ጭምር ሊከለሱ ታስበዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ድንጋጌ ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ነው፡፡

<u>የክልሎች ወሰንን በተመለከተ</u>፡- በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጎልቶ ያልወጡትም የክልሎች ወሰን ጥያቄዎችም ጭምር በኮሚሽኑ ተጠንተው (በራሱ ተነሳሽነት ጭምር) በቀጥታ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ቀርበው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡ ይሁንና በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 48 መሰረት የክልሎችን ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ በመጀመርያ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች ስምምነት ይፈታል፡፡ የሚመለከታቸው ክልሎች መስማማት ካልቻሉ ጉዳዩ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኛሉ፡፡ በመሆኑም ይህ ድንጋጌ በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 48 ስር የክልሎችን ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ በመጀመርያ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች ስምምነት ይፈታል የሚለውን መርሆ ይጥሳል፡፡

እንዲሁም ባለመብቱ መብቱ (ካለው) እንዲከበርለት ጥያቄ ባላቀረበበት ሁኔታ ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት የወሰን ጥያቄዎችን በማንሳት መርምሮ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣን አለው፡፡ በተጨማሪም ድንጋጌው ኮሚሽኑ የወሰን ጥያቄ የማቅረብ መብት ጨርሶ የሌለው አካልን ጥቆማ/ጥያቄን መነሻ ያደረገ ምርመራ እንዲያደርግ የሚያደርግ አካሄድ ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ድንጋጌ በሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 37፣ አንቀፅ 48 እና 62(6) ስር ስለፍትህ የመጠየቅና የማግኘት መብት የተደነገጉት ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን ይጥሳል፡፡

በተጨማሪም፣ እልባት ያገኙ የወሰን ጥያቄዎችን እንደገና ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት በማንሳት እንደገና አጥንቶ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣን አለው፡፡ ይህም ማናቸውም የአስተዳደር ወሰን ውሳኔ በማለት አመላክቷል፡፡ በመሆኑም እልባት ያገኙ የወሰን ጉዳዮች ጭምር ሊከለሱ ታስበዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ድንጋጌ ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ነው፡፡ ማለትም የሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 48ን የጣሰ ነው፡፡

<u>ራስን በራስ የማስተዳደርን ጉዳይ በተመለከተ</u>፡- በዚህ ድንጋጌ መሰረት ራስን በራስ የማስተዳደርን ጥያቄዎችን ጭምር በኮሚሽኑ ተጠንተው (በራሱ ተነሳሽነት ጭምር) ለፌደሬሽን ምክር ቤት ቀርበው ውሳኔ ያገኛሉ፡፡ ይሁንና በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 52(2)(ሀ) መሰረት እያንዳንዱ ክልል ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳደር የማዋቀር ስልጣን አለው፡፡ እንዲሁም በሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 50(4) መሰረት ክልሎች፤ በክልልነትና አስፈላጊ ሆነው በሚያገኙዋቸው የአስተዳደር እርከኖች የማዋቀር ስልጣን አላቸው፡፡ ስለሆነም ይህ የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌ እነዚህን የሕገ-መንግስቱ ድንጋጌዎችን የጣሰ ነው፡፡

እንዲሁም ባለመብቱ መብቱ እንዲከበርለት ጥያቄ ባላቀረበበት ሁኔታ ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄዎችን በማንሳት መርምሮ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣን አለው፡፡ ስለሆነም ይህ ድንጋጌ በሕገ-መንግስቱን አንቀፅ 37 እና አንቀፅ 39(3) ስር ስለፍትህ የመጠየቅና የማግኘት መብት የተደነገጉት ሕገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎችን ይጥሳል፡፡

በተጨማሪም ይህ የረቂቅ አዋጁ ድንጋጌ ኮሚሽኑ በራሱ ተነሳሽነት እልባት ያገኙ የራስን በራስ የማስተዳደርን ጥያቄዎችን እንደገና በማንሳት አጥንቶ የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የውሳኔ ሃሳብ የማቅረብ ስልጣን አለው፡፡ ይህም ማናቸውም የአስተዳደር ወሰን ውሳኔ በማለት አመላክቷል፡፡ በመሆኑም እልባት ያገኙ የራስን በራስ የማስተዳደርን ጉዳዮች ጭምር ሊከለሱ ታስበዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ይህ ድንጋጌ ኢ-ሕገ-መንግስታዊ ነው፡፡

### 3.3 የኮሚሽን አባላትና አሰያየም (አንቀፅ 7)

የረቂቅ ሕጉ አንቀፅ 7 የኮሚሽኑ አባላት ቁጥር በመንግስት እንደሚወሰንና የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ሌሎች አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚሰየሙ ይገልፃል። የረቂቁ አንቀፅ 14 ደግሞ ኮሚሽኑ በነፃነትና በገለልተኝነት እንደሚሰራ ይደነግጋል። ሆኖም በሰዎቹ አመራረጥ፣ ቁጥርና የስራ ሁኔታ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያልተገደበ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ኮሚሽኑ ነፃ ነው ሊባል የሚቻልበት አንድም ምክንያት የለም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የኮሚሽኑን ስብጥር

የሚፈልገውን ውጤት በሚያስገኝ መልኩ ሊያደራጅ ይችላል። ለኮሚሽን አባላት በስራ የመቆየት ዋስትና የሚመለከት ድንጋጌ በረቂቁ ውስጥ የለም። ይህ በመሆኑ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማንኛውምንም የኮሚሽን አባል እንደፈለገ ሊያነሳና በሌላ ሊተካ ይችላል ማለት ነው። ኮሚሽኑ ገለልተኛ የሚሆነው ገለልተኛነቱን የሚያረጋግጥ የህግ ማዕቀፍ ሲኖር እንጂ ገለልተኛ ነው ተብሎ ስለታወጀ ብቻ አይደለም።

### 3.4 የኮሚሽኑ የሥራ ዘመን (አንቀፅ 15)

የኮሚሽኑ የስራ ዘመን 3 ዓመት እንደሆነ በረቂቅ አዋጁ ላይ በግልፅ ሰፍሯል። በሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 48 እንደሰፈረው ፌደሬሽን ምክር ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ለመወሰን ሁለት ዓመት ድረስ መወሰድ እንደሚችል ተደንግጓል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚነሱ ሁሉም የወሰንና የማንነት ጥያቄዎች በሶስት ዓመት ውስጥ ለሚመለከተው አካል ይቀርባሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ጥያቄውን መቼና የት እንደሚያቀርብ የሚወስነው ባለጉዳዩ እንጂ ፌደራል መንግስት ባለመሆኑ፣ ጥያቄዎቹ በዚህ የጊዜ ገደብ ይቀርባሉ ቢባል እንኳን ኮሚሽኑ ይህን ሁሉ ጥያቄ በሁለት ሳምንት አንዴ እየተሰበሰበ ሁሉም ጉዳዮች በሶስት ዓመት የማያዳግም እልባት እንዲያገኙ ማድረግ ይችላል ማለት በህዝቦች መብት ማላገጥ ነው።

### 3.5 ጠቋሚዎችንና ምስክሮችን ስለመጠበቅ (አንቀጽ 17)

የኮሚሽኑ ተልእኮ ዘላቂ ሰላም በሚያረጋግጥ አገባብ የማንነትና የወሰን ጉዳዮችን ለመወሰን ሳይሆን የእውነት መሰረት በሌለውና የህዝብን ፍላጎት በማያንፀባርቅ ሂደት መሆኑ የሚያሳየው ሌላው አንቀፅ ጠቋሚዎችና ምስክሮችን በሚመለከት የያዘው ድንጋጌ ነው። ይህ ድንጋጌ ምስክሮችና ጠቋሚዎች እውነት የመናገር ግዴታ እንደሌለባቸውና የሆነ ያልሆነውን መረጃ ለኮሚሽኑ እንዲያቀርቡ የሚያበረታታ ያለተገደበ በህግ ያለመጠየቅ መብት አጎናፅፏቸዋል። ይህ አንቀፅ በከፊል ***"ማንኛዉም ሰው በኮሚሽኑ ፊትቀርቦ በሚሰጠው ቃል መሰረት ክስ ሊመሰረትበት እንደዚሁም የሰጠው ቃል በእርሱ ላይ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብበት አይችልም"*** በማለት ይደነግጋል። ኮሚሽኑ ኢትዮጵያ ውስጥ ወሳኝ በሚባሉና የሚልዮኖችን እጣ ፈንታ በሚወስኑ ጉዳዮች ላይ

የውሳኔ ሀሳብ የሚያቀርብ ነው። አይደለም በዚህ መጠን በአገር መፃኢ እድልና ሰላም ወሳኝ ድርሻ ባለው ጉዳይ ይቅርና በግለሰቦች መካከል በተፈጠረ አለመግባባት ላይ **ምስክርነት የሚሰጡ ምስክሮች እንኳን እውነት የመናገር ግዴታ** አለባቸው። አንድ ሰው ምስክር ሆኖ የመንግስትን ተቋም በመርዳቱ ጥበቃ ቢደረግለት ባልከፋ፣ **ወሽትም ብትናገር ማንም የሚጠይቅህ አይኖርም ብሎ በህግ ደረጃ ማበረታታት** ግን የለየለት ስርዓት አልበኝነት ነው። የሆነስ ሆነና ኮሚሽኑ ምስክር የሚጠራውና የሚሰማው እንዴት ይሆን? እውን የህዝብ አሰፋፈርና ፍላጎት በምስክር ሊረጋገጥ ይችላልን? ምስክር የሚያስፈልግስ ቢሆን ፌደሬሽን ምክር ቤት ፊት ቀርበው እንዲመሰክሩ ያልተፈለገው ለምንድ ነው? በወሰን የተወዛገቡት ክልሎችስ ምስክሮች እንዲያቀርቡ ይፈቀዳል? ክስ ያላቀረበ ወይም ያልቀረበበት ክልል እንዴት ይሆን በሂደቱ የሚሳተፈው? ወይስ ኮሚሽኑ ከሳሹንም ተከሳሹንም ተክቶ ሊከራከር፣ ከዛም ገለልተኛ ሆኖ ፍርድ ሊሰጥ ነው?

ይህ ድንጋጌ ለጠቋሚዎችና ምስክሮች ያለመከሰስ መብት አጎናጽፏል እንዲሁም ጠቋሚዎቹና ምስክሮቹ በገዛ ፋቃዳቸው የሰጡት ቃል በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደማይችል ደንግጓል፡፡ ሆኖም የሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 25 ድንጋጌ እንደሚያሳየው ሁሉም ሰዎች እኩል ናቸው፣ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሄር፣ ብሄረሰብ፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡ በመሆኑም ይህ ድንጋጌ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 25 የተደነገገውን የግለሰቦች የእኩልነት መብትን ይጥሳል፡፡

## 4 <u>*መደምደምያ*</u>

ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረበው ረቂቅ አዋጅ ይዘት በበርካታ ምክንያቶች ሕገ-መንግስቱን የሚፃረር ነው። ረቂቅ አዋጁ በሕገ መንግስቱ የሰፈረውን የህዝብ የስልጣን ባለቤትነት የሚንድ፣ የስልጣን ክፍፍል ቀመር በመጣስ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ስልጣን የሚሻማ፣ የማንነትና የወሰን ጥያቄዎች ሕገ-መንግስቱ ከሚያስቀምጠው ስርዓት ውጪ ለገለልተኝነታቸው እንኳን የህግ ጥበቃ በሌላቸው ጥቂት ሰዎችና በጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲወሰኑ የሚያደርግ፣ ክልሎች በሕገ-መንግስቱ የተሰጣቸውን ስልጣን የሚሸረሽር፣ ሕገ-መንግስቱ ለብሄር

ብሄረሰቦች የሰጠውን መብት የሚነፍግና በአጠቃላይ በሕገ-መንግስቱ የሰፈረውን ስርዓት የማይከተል በመሆኑ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም። የሕገ-መንግስቱ አንቀፅ 9 ማንኛው ህግ ሕገ-መንግስቱን የሚፃረር ከሆነ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው ይደነግጋል። ስለዚህ ይህ አዋጅ ከላይ በተገለፁት ምክንያቶች ሕገ-መንግስትን የሚጥስ በመሆኑ ኮሚሽኑም ሆነ የሚሰጣቸው ውሳኔዎች እውቅና ሊሰጣቸው አይገባም።

አዋጁ ህገ መንግስቱን የሚፃረር በመሆኑ የክልሎችን መልካም ግንኙነት ይበልጥ ከማሻከር አልፎ በብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች በሕገ-መንግስታዊ ስርዓቱ ጥርጣሬና አለመተማመን እንዲያድርባቸው የሚያደርግ ነው። ይህ አዋጅ ዘላቂ ሰላማችንን የሚያደፈርስ ነው፤ አገራችንን የማልማት የጋራ ራዕያችንን የሚያጨልምም ነው። **ለማጠቃለል ያህል፡-**

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ የሆነውን ሕገ-መንግስት የሚጥሰውን ይህንን ረቂቅ አዋጅ ውድቅ እንዲያደርገው እንጠይቃለን፡፡
2. እንዲሁም የፌዴሬሽን ምክር ቤትም ይህ ረቂቅ አዋጅ ሕገ-መንግስቱን የሚጥስ መሆኑን አውቆ ተቃውሞውን በማሰማት ሕገ-መንግስቱን የማስከበር ኃላፊነቱን እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡